የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፬
አዲስ አበባ ኅዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 4
ADDIS ABABA - 18th November, 1999

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፹፪/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደግል ስለማዛወር የወጣ /ማሻሻያ/ አዋጅ ........................................ ገጽ ፩ሺ፩፻፸፭

## CONTENTS

Proclamation No. 182/1999
Privatization of Public Enterprises (Amendment) Proclamation ........................................ Page 1175

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፹፪/፲፱፻፺፪
## የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደግል ስለማዛወር የወጣውን
## አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር የወጣውን አዋጅ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደግል ስለማዛወር የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩፻፹፪/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደግል ስለማዛወር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፮/፲፱፻፺፩ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩/ ከአንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፬) በኋላ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፭ እና ፮ ተጨምረዋል፤

"፭/ የንግድ ሕግ አንቀጽ ፭፻፵፮ ንዑስ አንቀጽ (፩)–(፬) ድንጋጌዎች ቢኖሩም ኤጀንሲው አንድን የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማኅበርነት እንዲለወጥ ሲያደርግ ወደ አክሲዮን ማኅበሩ የሚተላለፈውን ሀብትና ዕዳ እንዲሁም የአክሲዮን ማኅበሩን ካፒታል የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል።

## PROCLAMATION NO. 182/1999
## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE PRIVATIZATION OF PUBLIC ENTERPRISES PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Privatization of Public Enterprises Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Privatization of Public Enterprises (Amendment) Proclamation No. 182/1999."

2. *Amendment*

The Public Enterprises Privatization Proclamation No. 146/1998 is hereby amended as follows:

1) The following new Sub-Articles (5) and (6) are added after Sub-Article (4) of Article 5:

"5/ Notwithstanding Article 546 Sub-Articles (1) – (4) of the Commercial Code, the Agency shall, in converting a public enterprise into a share company, have the power to determine the assets and liablilities of the enterprises that may be transferred to the share company and fix its capital.

፮/ ወደ አክሲዮን ማኅበርነት የተለወጠ የመንግሥት የልማት ድርጅት አክሲዮን ማኅበሩ እንደተመዘገበ ሕጋዊ ሕልውናው ያከትማል።”

፪/ የአንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሠርዟል።

፫/ የአንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል።

“፩/ ወደግል ይዞታ የተዛወረ የልማት ድርጅት ርክክቡ እንደተፈጸመ ሕጋዊ ሕልውናው ያከትምና መብትና ግዴታዎቹ ወደ ገዥው ወይም ገዥው ወደ አቋቋመው ኩባንያ ይተላለፋሉ።”

፬/ ከአንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) በኋላ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተጨምረዋል፤

“፫/ የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማኅበርነት ሲለወጥ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭(፭) መሠረት ስለሀብትና ዕዳ መተላለፍ በሚሰጠው ውሳኔ ወደ አክሲዮን ማኅበሩ ሳይተላለፍ የሚቀረው ሀብትና ዕዳ ለባለአደራ ቦርዱ ይተላለፋል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰዱ ንብረቶች በወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፲/፲፱፻፹፯ መሠረት በኤጀንሲው ውሳኔ ለቀድሞ ባለቤቶቻቸው የሚመለሱ የልማት ድርጅቶች መብትና ግዴታ መተላለፍን በሚመለከትም በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናሉ።”

፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

6/ An enterprise converted into a share company shall cease to exist upon registration of the Share Company''.

2) Sub-Article (4) of Article 7 is deleted.

3) Sub-Article (1) of Article 13 is deleted and replaced by following new Sub-Article (1):

1/ A privatized enterprise shall cease to exist upon completion of handover and its rights and obligations shall be transferred to the buyer or to the company established by the buyer.''

4) The following new Sub-Articles (3) and (4) are added after Sub-Article (2) of Article 13:

''3/ The residual assets and liabilities following the decisions of the Agency in accordance with Article 5 (5) of this Proclamation on the transfer of assets and liabilities of a public enterprise being converted into a share company shall be transferred to the Board of Trustee.

4/ The Provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article shall similarly be applicable with respect to the transfer of rights and obligations of public enterprises returned to their former owners by the decision of the Agency pursuant to Proclamation 110/1995.''

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 18th day of November, 1999.

Done at Addis Ababa, this 18th day of November, 1999.

NEGASO GIDADA(DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE